# “ሁሉም ቢተባበር፤ ሁሉም ቢረዳዳ…”

ደስታው አንዳርጌ (ዶ/ር)

ሰኔ ፪ ሺ ፺ ዓም

መረዳዳትና መተባበር እንደልባችን እየለዋወጥን የምንጠቀማቸው ቃላት ናቸው። የአዲስ አበባ ምፅዋት ጠያቂ ‘ነብሱ የትራንስፖርት ኀሉብኝ ነው፤ ያለህን ተባበረኝ’ ሲልህ ርዳታንና ትብብርን እያቀላቀለ ነው። ነገር ግን በሁለቱ ፅንሰ ሀሳቦች መካከል ያለው ልዩነት መሰረታዊ ነው። በሁለቱ መካከል ያን ያህል ዝምድና የለም። መረዳዳት የጋራ ራዕይን አይጠይቅም። የመረዳዳት አይነተኛ መገለጫ ከሁለቱ ወገኖች አንዱ አቅመቢስ በመሆኑ (ወይም አቅመቢስ ነኝ ብሎ ስላመነ)የሌላኛውን ርዳታ የሚሻ መሆኑ ነው። ስለዚህ አቅም ያለው የመንፈስ ርካታ ለማግኘት፣ መንግስተ ሰማያት ለመግባት በማሰብ ወይም ደግሞ ከመሰሪ ስሌት ተነስቶ እጁን ይዘረጋለታል። በውጤቱ የለጋሹ አቅም ከነበረበት ዝቅ ወይ ከፍ ሊል ይችላል። በአንጻሩ ተረጂው ህይወቱን ያቆያል፤ በአብዛኛው ከተረጅነት ግን አይወጣም። እንዲያም ሲል ከተረጅነት የማይወጣበት ቀለበት ውስጥ ሊወድቅ ይችላል። ኢትዮጵያን ይመለከቷል። መተባበር በአንጻሩ ሁለቱም ወገኖች አቅም እንዳላቸው በመረዳት አቅማቸውን ቢያቀናጁ ከሁለቱም አቅም ድምር በላይ የሆነ ታላቅ ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ከመገንዘብ ይጀምራል። ሁለተኛው መሰረታዊ ልዩነት መተባበር የሁለቱንም ወገኖች ጥቅምና አስተዋጽኦ ይመለከታልና በሁለቱም ወገን ሀላፊነትና ዲሲፕሊን ይጠይቃል። ርግጠኝነትና ተተንባይነት መገለጫወቹ ናቸው። በአንጻሩ መረዳዳት ዘፈቀዳዊ ነው። ሲጀመር ተረጂው ሀላፊነት የለበትም። ረጂውም ቢሆን ደስ እንዳለው ነው፤ ከፈለገ ይረዳሀል ካልፈለገ አይረዳህም። ከምንም አይነት ግዴታና ዲሲፕሊን ጋር አይያያዝም። ስለሆነም ርግጠኛ መሆን አትችልም። ሶስተኛው መተባበር በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ነው። ሁለቱም ወገኖች ቢተባበሩ የሚያገኙትን ጥቅም አስልተው የሚገቡበት ነው። መረዳዳት በአንጻሩ ስሜታዊ ወይ ደግሞ ዕምነታዊ ነው። አሳዘነኝ ዳቦ ጣልሁለት። ወይ ደግሞ ቄሱ ምጽዋት ያጸድቃል ሲሉ ሰምቸ። የመጨረሻው መረዳዳት የስሜት ጉዳይ ነውና በተፎካካሪወች መካከል አይታሰብም፤ ትብብር ግን ወደኋላ እንደምናየው በጥቅም እንጂ በፉክክር ወይ በሌላ ምክንያት አይገደብም።

እንዲያም ሲል መረዳዳትና መተባበር ተጻራሪ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ ኢትዮጵያውያን በመረዳዳት አንታማም። ካፒታሊዝም ባልገነነባቸው ማህበረሰቦች እንደሚታየው ሁሉ በአገራችን ጠንካራ የመረዳዳት መንፈስ ይታያል። ወገን ሳለ፤ ጎረቤት ሳለ በደስታ በሀዘን ማንም ሰው ብቻውን አይቆምም። በመተባበርስ? ምን ትስቱት፤ ምን እነግራችሁ። እንደመተባበር የሚቸግረን ነገር ከቶ ምን አለ? ግፍ፣ ጭቆና፣ ውርደት፣ ስደት፣ ችጋር፣ ስቃይ፣ ሞት ሁሉ ተደማምረው የመተባበርን ያህል አይከብዱንም። ይኼ መላምት አይደለም። ሀቅ ነው፤ መራራ ሀቅ! የምንራበው የኢትዮጵያ ምድር ሰብል ስለማያበቅል አይደለም። አንዳንዶች እንደሚሉት ሰነፎች ሆነንም አይደለም (ደሀውን ገበሬ ተመልከቱ፤ የምሳ ሰአት አያውቅም። ተማረ የሚባለውም ቢሆን አገሩ ላይ ነው እንጂ ባለጉዳይ ለማናገር የሚጀነነው ፈረንጅ አገር ሲሄድ ክብሬ ቅብጥርሴ ሳይል እንደ እንዝርት ነው የሚሾረው)። የምንሰደደው አገራችን ጠቦን አይደለም። ኋላቀር የሆነው ጭንቅላታችን እንደሌላው ህዝብ ማሰብ ስለማይችል አይደለም። በያገሩ የምንሰለፈው የአሜሪካ ወይ ደግሞ የሌላ አገር መንግስት የኛ ጉዳይ በእውነት አሳስቦት መፍትሄ ስለሚሰጠን አይደለም። ኢትዮጵያ ውስጥ ቁጥር ስፍር የሌለው የፖለቲካ ቡድን ያለው በመካከላቸው የማይታረቅ የአይዲዮሎጂ ልዩነት ስላለ ወይም እንዲያ ተበጣጥሰው መቸም የትም እንደማይደርሱ አጥተውት አይደለም። በአጠቃላይ ከችግር የማንወጣው ተረግመን፣ ዕጣ ፈንታችን ሆኖ ወይ ደግሞ ያ መከረኛ ሰይጣን ተመቅኝቶን አይደለም። ችግራችን ከሌላው ህዝብ የገዘፈ ሆኖም አይደለም። ወይ ደግሞ እኛ በራሳቸን የራሳችን እጣ ለመቀየር አቅም ስለሌለን አይደለም። ስለማንፈልግ ብቻ ነው። የማንፈልገው ደግሞ መተባበር ስለሚጠይቅ ነው። እንደ እስራኤላዊያን፣ እንደ ጃፓናዊያን፣ እንደቻይናዊያን፣ እንደሌሎቹም የጋራ ራዕይ አንግቦ መተባበር። ያ ከምንም በላይ ያዳግተናል። ስለሆነም ፖለቲከኞቻችን(ፖለቲካ በሌለበት ፖለቲከኛ ካለ ማለቴ ነው) ‘ወይ ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ’ ስትሏቸው ያሳዝኑኛል። በባህላችን የሌለውን የመተባበር መንፈስ ከየት ያመጡታል በሚል። እስቲ አንድ ጥያቄ ላንሳ። ባለፉት አርባ አመታት ስንት የፖሊቲካ ድርጅቶች ተመስርተዋል? ስንትስ የሲቪክ ማህበራት ተቋቁመዋል? ምን ያህል የሙያ ማህበራት ተመሰረቱ? እስቲ ከዚያ ውስጥ ይረባል የምትሉትን ጥሩ። አገኛችሁ? ካገኛችሁ መልካም። ካልሆነ ግን ችግሩ ጠለቅ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ይመስለኛል። እንደሚታየኝ የባህል አብዮት ያስፈልገናል።

በአንጻሩ በኢኮኖሚ የበለጸጉት ህዝቦች በመተባበር የሚሆናቸው የለም፤ መረዳዳትን ግን የኛን ያህል አያውቁትም ወይ አይፈልጉትም (ከናቹረል ሰሌክሽን አስተምህሮት ጋር አይሄድማ)። በነሱ ርዳታ እየኖርን እንዴት ርዳታ አያውቁም ብለህ ታማቸዋለህ ትሉኝ ይሆናል። ርግጥ ነው እንደ አገር 'የኔ ቢጤ' ነን። የሚረጥቡን ደግሞ በኢኮኖሚ የበለጸጉት አገራት ናቸው። የሚረጥቡን ግን ስንራብ እያዩ አንጀታቸው አልችል ስላለ አይደለም። ስለሚያዋጣቸው መሆኑን በሌላ ክታብ ለማሳየት ሞክሬአለሁ።[1] እነሱ በዋናነት የሚያምኑት በመተባበር እንጂ በመረዳዳት አይደለም። ስለዚህ በመተባበር ላይ ስላላቸው ብልህነት እናውጋ።

ከላይ እንዳልሁት የሚተባበሩት ሳይንሳዊ የጥቅም ስሌት አርገው ነው። ስለዚህ ያሸንፋሉ። የሚተባበሩት በጎሳ አጥር ውስጥ አይደለም(በጎሳ ወይ በሀይማኖት ታጥሮ መራኮትን ለኛ ለኋላቀሮቹ ሲተውልን በደስታ እንዲያም ሲል ከማበረታቻ ጋር ነው)። ትብብራቸው በአገር ደረጃም አይወሰንም። በዘላቂ ጥቅም እንጂ ድንበር አይወስነውም። አንድ ምሳሌ ልጥቀስ። እስከ ፪ኛው የአለም ጦርነት ድረስ እንግሊዝና ፈረንሳይ የአለም ጌቶች ነበሩ። ሂትለር ሁለቱንም ጉድ አደረጋቸው እንጂ። ፈረንሳይ በዝረራ ተሸነፈች። (አጼ ቴወድሮስ ባህሯን ተማምና ነው እንጂ እስቲ ሜዳ ላይ ትግጠመኝ ያሏት) እንግሊዝ ግን ሜዳ ላይ ብትሸነፍም ባህሯን ተገን አርጋ መከላከሏን ቀጠለች (ለካስ ባህር ከግመል ማጠጫነት ያለፈ ፋይዳ አለው አትሉም?!)። አንድ ነገር ግን ግልጽ ሆነ፤ ሁለቱም ከዚያ በፊት ያደርጉት እንደነበረው አለምን መጫወቻ ማድረግ አይችሉም። ምክንያት? አንድ፤ ሁለቱም በጦርነት ደቀዋል። ሁለተኛውና ዋናው ግን አሁን አሜሪካና ሶቭየት ህብረት የሚባሉ ሀያላን ተፈጥረዋል (ጦርነቱ አውሮፓውያንን ሲያደቅ የሁለቱን ጡንቻ በታሪክ ባልታዬ ሁኔታ እጅግ አፈረጠመው፣ ያለው ማማሩ)።

ነገር ግን አዳዲስ ልዕለ-ሀያላን መፈጠራቸው በራሱ ለጭቁኖች ብዙ ፋይዳ አልነበረውም። ልዩነት ያመጣው አዳዲሶቹ ልዕለ-ሀያላን እንደነ እንግሊዝ ያለ ቅኝግዛት ያልነበራቸው መሆኑ ነው። በመሆኑም የአለምን ጥሬሀብት ከመበዝበዝ አንጻር የእነእንግሊዝን ያህል እድል አልነበራቸውም። በመሆኑም ሶቭየት ህብረት ከመጀመሪያውም የለየላት የቅኝ ግዛት ተቃዋሚ ስትሆን አሜሪካም የቅኝግዛት ማብቃት ይጠቅማታልና ከጥቅሟ ተነስታ እነ እንግሊዝን ማሳመን ነበረባት (ሁለተኛው ጦርነት ባይኖር የአፍሪካ የነጻነት ጥያቄስ ምን ይሆን ነበር?)። ሩዝቤልትና ቸርችል መርከብ ላይ ተገናኝተው ሲወያዩ ያለፈው አይነት ኢምፔሪያሊዝም የመቀጠል እድል እንደሌለው ተግባቡ። ይልቁንም የቦልሸቪኮች ፕሮፖጋንዳ አለምን ሳያሸፍተው አሜሪካ የአለም ጌትነቱን ከእንግሊዝ ተረክባ አዲስ አይነት ኢምፓየር እንድትመሰርት ተስማሙ። እንግሊዝ በትረመንግስቱን (የመካከለኛው ምስራቅ የነዳጅ ሀብት መቆጣጠርን ጨምሮ) ለአሜሪካ ብታስረክብም አልተከፋችም። ርግጥ ነው አሁን ፉክክሩ በምዕራብና ምስራቅ ጎራ ብቻ አይደለም፤ አሜሪካ እኮ ከኢኮኖሚ ስሌት ተነስታ እንግሊዝን ከቅኝ ግዛት ጉልቷ ነቅላ ራሷ ለመተካት ነው አላማዋ። ግን እየረፎካከሩም የጋራ ጥቅማቸውን አስተዋሉ። እንግሊዝኛ የአለም ቋንቋ ይሆናል። የኒዮክሌር ቁልፍ ከሚኖርህ ደግሞ ፕሮፖጋንዳን መቆጣጠር ይበልጣል። አለም ሁሉ የነሱን ቋንቋ ለመማር ይከፍላል፣ የነሱን ቋንቋ ማወቁን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ይከፍላል፣ የነሱን ስፖርትና ፊልም ለማየት ይከፍላል፣ ሰወች ሁሉ ስለራሳቸው ሳይሆን ስለነሱ ሲያወሩ ውለው ያድራሉ (ልክ አዲስ አበባ ሬዲዮው፣ ጋዜጣው፣ ወጣቱ፣ ሽማግሌው፣ አኪሙ፣ ሾፌሩ፣ ወዘተ ስለ እንግሊዝ ኳስ ሲያወራ መሽቶ እንደሚነጋለት ማለት ነው)፣ ዜጎቻቸው የትም አገር ሲሄዱ እንደንጉስ ይታያሉ፣ እያለ ይቀጥላል። ወቅታዊው ጉዳይ ግን አሜሪካና እንግሊዝ (ከካናዳ እስከ ኒውዚላንድ ጫፍ ያሉትን ጨምሩ) እስከተባበሩ ድረስ አለምን ለመቆጣጠር በተለይም ባስደንጋጭ ፍጥነት የገሰገሰችውን፣ የሚቋቋመው የጠፋውን ሂትለርን ድባቅ የመታችውንና ፀረ-ኢምቴሪያሊዝም የሆነ አደገኛ አቋም ይዛ ሶስተኛውን አለም ብቻ ሳይሆን የአውሮፓ ድሆችና ተራማጆችን ያሳመጸችውን ሶቭየት ህብረትን ለመመከት አያዳግትም። ትልቁን ጥቅማቸውን ተመለከቱና ተስማሙ። ይኸው አሁንም አለምን ይቆጣጠራሉ (እነ ሂውመን ራይትስ ወችና አምነስቲ የተባሉ ድርጅቶቻቸው ሳይቀር የትኛውንም መንግስት የመቆጣት ስልጣን እንዳላቸው ነው የሚሰማቸው)። እኛ ከምነናቆርባቸው 'አርብተን እያደርን አርሶ አደር ተብለን ተሰደብን' አይነት ጥቃቅን ጉዳዮች ጋር አነጻጽሩና ርማችሁን አውጡ። ከተቻለ (ፈቃደኛ ከሆንን ማለቴ ነው) ግን እንማር። ችግሩ የአቅም ሳይንሆን የፈቃድ ጉዳይ ነው ብዬ አምናለሁና።

ሰላም ሁኑ።

---

[1] ደስታው አንዳርጌ፣ 'ዓለምአቀፍ  ርዳታና ፖለቲካው' http://www.ethiomedia.com/100leads/ethiopia_aid_and_politics.pdf